# የአባላዘር ተላላፊ በሽታዎች እውነት ነገሮች

Herpes - Amh

## ሄርፒስ
## (ከ ሄርፒስ ሲምፕለክስ ቫይረስ 1 ና 2 የሚመጣ፣ ኤች-ኤስ-ቪ)

### የበሽታው ምልክቶች

ያባላዘር ሄርፒስ ምልክቶች፣

- በቫይረሱ ከተለከፉ ከ2 እስከ 30 ቀን በኋላ
- ቡንጅ መሰል እባጮች በብልት፣ አፍና ቂጥ መውጣት
- እባጮቹ ከተከፈቱ 1-2 ሳምንት በኋላ ይድናሉ
- ቁስሎቹ ሴት ብልት ውስጥ ሊደበቁ ይችላሉ
- መጀመርያው የሚወጡ ቁስሎች በጣም ሃይለኛ ሲሆኑ፣ ቀጥለው የሚወጡት ግን መጠነኛ ናቸው
- ቁስል ሊወጣ ሲል ማሳከክና ማቃጠል ይጀምራል
- መጀመርያ ማመም ሲጀምር ትኩሳት፣ ራስምታትና የጉሮሮ ማበጥ ይጀምራል
- ቁስሉ ይሄዳል፣ በሽታው ግን ይቀራል
- ቁስሎቹ ሊመለሱ ይችላሉ፣ ነገር ግን ከበፊቱ የተሻሉ ናቸው

### መተላለፍ

ያባላዘር ሄርፒስ የሚተላለፈው፣

- በወንድ ብልት ግብረስጋ
- ባፍ ግብረስጋ
- በፊንጢጣ ግብረስጋ
- የበሽተኛ ቁስል በመንካት
- ከበሽኛ እናት አዲስ ወደተወለደ ሕጻን
- ቁስል ሳይኖር በቫይረስ ሊተላለፍ ይችላል

### ጣጣውና የሚያስከትለው ችግር

የባላዘር ሄርፒስ የሚያስከትለው ችግር፣

- የሄርፒስ ቁስሎች እንደ ኤች-አይ-ቪና ሌሎች ጀርሞች በቀላሉ እንዲገቡ ምቹ ይሆናል
- እየተመላለሰ በጣም ያሰቃያል

የአባላዘር ሄርፒስና እርግዝና፣

- እናቶች ለሚወለዱ ሕጻናት ያጋባሉ
- በሽታው አዲስ በተወለዱ ሕጻናት ሞት፣ ያንጎል፣ ሳንባና ጉበት ብልሽት ልያስከትል ይችላል
- አብዛኞቹ ተመላላሽ ሄርፒስ ያላቸው እርጉዞች ጤነኛ ህጻናት ይወልዳሉ
- የመጀመርያ ደረጃ በሽታ ካላቸው እናቶች የሚወለዱ ሕጻናት የሚያስከትለው ጉዳት በጣም የባሰ ነው

### መከላከል

የአባላዘር ሄርፒስን መዛመት ለመቀነስ የተሰጡ አስተያየቶች፣

- የአባላዘር ቁስል ኮንዶም መከላከያ በተደረገላቸው አካባቢ ነው የሚወጡት፣ መከላከያ ባልተደረገላቸው ቦታዎችም ሊወጡ ይችላሉ። የላተክስ ኮንዶም የሄርፒስ በሽታን ሊከላከሉ የሚችሉት፣ የበሽታው ቦታ በኮንዶም ከተሸፈነ ብቻ ነው።
- በሴት ብልትና ፊንጢጣ ግብረስጋ ኮንዶም ይጠቀሙ
- በወንድ ብልትና አፍ ግብረስጋ ኮንዶም ይጠቀሙ
- የሴት ብልት ግብረስጋ ባፍ ካደረጉ ኮንዶሙን በሁለት በመክፈል ይጠቀሙ
- የግብረስጋ ተካፋዮችዎ ይቀንሱ
- የአባላዘር ሄርፒስ ካለዎት ሃኪም ወይም በሌላ የህክምና አገልግሎት ይመርመሩ
- ከታመሙ የግብረስጋ ተካፋዮችዎ ያስታውቁ
- እርጉዝ ከሆኑና ካሁን በፊት ታመው ከነበረ ለዶክተር ያስታውቁ
- ምንም ግዘም፣ ቁስል ካለው ሰው የግብረስጋ ግንኙነት አያድርጉ

### ሕክምና

የአባላዘር ሄርፒስ ሕክምና፣

- ሕክምና የለውም፣ በሽታው እስከሞት ድረስ ይቆያል
- በሽታው እንዳይመለስ በየቀኑ መድሃኒት መውሰድ ያስፈልጋል
- እንደገና ለታመሙት፤ ምንም ለውጥ ስለማያስመጣ፣ ሕክምና አያስፈልግም
- እንደገና ለታመሙት ስቃዩን የሚቀንሱ አንዳንድ እርምጃዎች አሉ


ለተጨማሪ ማብራርያ በሚከተለው ይጠይቁ፣

Infectious Disease Epidemiology, Prevention and Control Division
STD and HIV Section
Minnesota Department of Health
P.O. Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
(651) 201-5414; (651) 201-5797 TTY

Minnesota Family Planning and STD Hotline
1-800-783-2287 ድምጽ /TTY

CDC National STD and AIDS Hotlines
1-800-227-8922; 1-800-243-7889 TTY

CDC National Herpes Hotline
(919) 361-8488